# የጎንደር ሕብረት

## አገር ያለ መሪ፤ ሕዝብ ያለ ተቆርቋሪ!

በቀደሙት ሃያ አራት ዓመታት፤ አገራችን ኢትዮጵያ፤ ከራሷ በበቀሉ ከሃዲዎች እጅ መውደቋን ሥናወግዝ ብንቆይም፤ ዛሬ ግን ፈጽሞ! ከሰው ተራ የወጡ የአውሬ መሪዎች እጅ እንዳለች ያረጋገጥንበት ወቅት ላይ ደርሰናል።

በማንኛውም ዓለምም ያሉ መሪዎች፤ ያለ ተቃውሞ ሕዝባቸውን የሚመሩበት አገር ቀርቶ፤ ዓለም ራሷ የተፈጠረችው በቅራኔዎች ውሥብሥብ ንጥረ ነገሮች ነው። ሆኖም፤ የማንም ዓለም መሪዎች፤ ህዝባቸው በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ አደጋ ሲጎዳ፤ በጠላት ሲጠቃ፤ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እና ቅሬታ ለሕዝባቸው ተቆርቁረው፤ አገራቸውን ወክለው ፈጥነው በመድረሥ ለሚወዷቸው ጥብቅናቸውን፤ ለሚቃወሟቸው እርህሩህነታቸውን በማሳየት የመሪነት ኃላፊነታቸውን እና ብቃታቸውን በማረጋገጥ አገር ያሥከብራሉ፤ ወገን ያኮራሉ፤ ታሪክ ይሰራሉ። ይህ ሲሆን፤ አገር መሪ አላት፤ ሕዝብም ተቆርቋሪ አለው ያስብላል።

እኛ ግን እንደ ዜጋ የሚቆረቆርልን መሪ ቀርቶ፤ በኛው በራሳችን መከፋፈል እና መለያየት ክፋት እግዚአብሔርም ርቆናል!! መከራ እና ሥቃያችን በዝቷል!! ውድ ልጆቻችን፤ የአገራቸውን ግፈኛ የአውሬ መሪዎችን ሥራአት መሸከም ሥለተሳናቸው፤ የሚወዷት አገራቸውን እና የሚዎዷቸውን ቤተሰቦቻቸውን በመተው ሥደትን መረጡ። እንደ አውሬ በባዕዳን እጅ ተቀጠቀጡ። እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ እንደ በጎች በጨካኞች እና በአረመኔዎች እጅ ታረዱ። እንደ እንጨት በሳት ተቀጣጠሉ። እኛም፤ ይህን ያዬ ህሊናችን እሥከ ወዲያኛው ድረስ፤ በመታረዳቸው ልባችን ታርዷል። በመቃጠላቸው ልባችን ተቃጥሏል። ኧረ! ምንሥ ህሊና ይረሳዋል!!

ከሁሉም በላይ እጅግ የሚዘገንነው፤ ዓለም ያለምንም ማሥረጃ በሥዕላችን (በገጸ ባህሪያችን) በወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውን አሰቃቂ ድርጊት እያወገዘ፤ አውሬዎቹ የአገራችን መሪዎች “ዜጎቻችን ሥለመሆናቸው እያጣራን ነው” በማለት ሲሳለቁብን ከማየታችን ባሻገር፤ በትናንትናው (04/22/2015) ዕለት ደግሞ፤ በአዲስ አበባ ከተማ ሃዘናቸውን ሊገልጹ፤ እምባቸውን በጋራ ሊያፈሱ አደባባይ በወጡት ወገኖቻችን ላይ የተወሰደው አረመኔያዊ ድብደባ፤ በሊቢያ ካሉት አራጅ አረመኔዎች የማይተናነሥ አሳፋሪ ተግባር ማየታችን እና የረድዋን ሁሴን “ሁሉም ሰው ያለችግር ወደቤቱ ተመልሷል” የሚለው የቴሌቭዥን አይን ያወጣ የተለመደው የወያኔው ሆዳም ውሸት ነበር። ታድያ ከዚህ በኋላ ምን እሥኪመጣ ነው እኒህን ግፈኞች የምንታገሳቸው እና አገር እየጣልን የምንሰደደው? ሞትን እና መከራን ሸሽተን፤ ከሰው አገርም ሄደን ማምለጥ ካልቻልን፤ ለምን ግፈኛ የአውሬ መሪዎችን በልተን በቅድሥና አገራችን ላይ አምርብን አንሞትም?

ባጭሩ፤ ለዚህ ሁሉ የግፍ እና የመከራ ታሪክ ተጠያቂው፤ አውሬው ወያኔ መራሹ አገር እና ወገን አጥፊው ሥራአት ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፤ በሥሩ የተኮለኮሉት የወገኖቻችን ህይወት በደላላነት ተግባር ተሰማርተው መሥመር ዘርግተው ለባዕዳን በመሸጥ፤ ሰማይ ጠቀሥ ፎቅ በመሥራት በንጹኋን ደም የተነከሩት ቀራጮች መሆናቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ተገንዝቦ፤ ከማንኛውም በፊት የልጆቹን ደም እንዲበቀል ጥሪያችን እናሥተላልፋለን።

# የጎንደር ሕብረት

ዛሬ፤ በደቡብ አፍሪቃ በግፍ ሲቃጠሉ፤ በሊቢያ በጭካኔ ሲታረዱ፤ በየመን በርሃ በግፍ ሲጨፈጨፉ፤ ሁሉንም አልፈው ውቅያኖሥ ሊያቋርጡ ሲሞክሩ ውሃ የበላቸው በዓለም ዙሪያ የዜና መገናኛዎች ሲታውሱ፤ ሁሉም የተለጠፈባቸው የመለያ ቁጥር (ታርጋ) "ኢትዮጵያውያን" የሚል ነው። ይሕ ደግሞ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ልዩነታችን አሥወግደን በጋራ እንድንቆም እና የችግራችን ራሥ የሆነውን የወያኔ ሥራአት እንኮታኩተን በመጣል፤ በምትኩ እንደ ሰው ተከብረን በነጻነት፤ በእኩልነት እና በጋራ የምንኖርባትን ዲሞክራሲያዊት አገር ገንብተን ለተተኪው ትውልድ እንድናስተላልፍ የተላለፈ ህይውት የተከፈለበት ልዩ መልክት ነው።

ስለዚህም፤ በመላው ዓለም ዙሪያ ያላችሁ፥

1. የማንኛውም ኃይማኖት አባቶች እና ተከታዬች፤ በየመን፤ በደቡብ አፍሪካ፤ በሊቢያ ህይወታችው በግፍ እያለፈ ላሉት እና በውቅያኖስ ውስጥ ሰምጠው ለቀሩት ወገኖቻችን የህልፈተ ህይወት ጸሎት። በአረመኔዎች እጅ ለወደቁት እግዚአብሄር ዓምላክ እንዲታደጋቸው የጀመራችሁት ጸሎተ እና ምህላ እንድታራዝሙ እና እስከ መጨረሻው ከህዝባችሁ ጎን እንድትቆሙ፤

2. በምንም ይሁን በምን፤ በተለያዩ የድርጅት ፕሮግራም የተደራጃችሁ ወገኖች፤ ምሁራን እና አዋቂዎች፤ ያለ መሪ ያለችዋን አገራችን፤ ያለተቆርቋሪ የግፍ እና የመከራን ጽዋ የሚጎነጩ ወገኖቻችንን ለመታደግ፤ የዚህ ሁሉ ግፈ አንዱ ምክንያት የኛም በሕብረት እና በአንድነት አለመቆም መሆኑን በመገንዘብ ልዩነታችን አሥወግደን በጋር በመቆም መታገል እና ለመላው የኃያላን መንግሥታት፤ ለሰባዊ ድርጅቶች፤ ለሥደተኛ ጉዳይ ድርጅቶች አቤቱታ በማቅረብ፤ በሊቢያ በርሃ ለአደጋ የተጋለትጡትን የምንታደግበትን መንገድ ለመፈለግ እንድንተባበር፤

3. በአጠቃላይ አገር ውጭም ይሁን ውሥጥ ያላችሁ ወገኖቻችን፤ ከላይ እንደገለጽነው፤ አገር እንደ አገር፤ ህዝብም እንደ ዜጋ ለመኖር ያለመቻሉ ምክንያት አሥከፊው እና አውሬው የወያኔ ሥራአት መሁኑን ተገንዝበን፤ ያለ ምንም ልዩነት በጋራ በመተባበር የሥራአቱን ፍጻሜ እንድናፋጥን ጥሪያችን እናሥተላልፋለን።

እግዚአብሔር በአሰቃቂ ሁኔታ በግፍ ለታረዱት እና በቁም ለተቃጠሉት ወገኖቻችን፤ መንግሥተ ሰማየትን እንዲያውርሥልን፤ ለቤተሰቦቻቸው እና ለቅርብ ጓደኞቻቸው፤ መጽናናትን እዲሰጥልን እንመኛለን።

በግፍ በመላው የዓለም ዙሪያ እየፈሰሰ ላለው ደም፤ አውሬው የወያኔ ቡድን ተጠያቂ ነው!!!

ጎንደር ሕብረት።